

# የፍቅር ጌታ ብላቴ

*ሥርጉተ ሥላሴ*
*የካቲት 18 ቀን 2001 ዓ.ም.*

እንደምን አለህ አባቴ
የሥነ ጥበብ ጉልላቴ
ዬስምንትዮሽ መቀነቴ።

የፀጋ መሰረት ሀውልቴ
የዕምነት የትውፊት ቤቴ
የቅኔው እጨጌ ህብስቴ።

የአፍሪካዊነት ልዩ ቀንዲሌ
የእማ ፍፁም ጌጥ ድባቤ
የደሜ ህብር ዐውደ ዘቤ።

የፍቅር ጌታ ብላቴ
የቀስተደመና ጠበብቴ
የሰላም አባት ብሩህ ህብስቴ።

አልሞትክም አለህ ፀግሽ
ቁርባነ ዘርህ እንባ አባሽ
ዓምደ ፈጠራህ ህሊና አራሽ።

*ዙሪክ ኦውሮፕላን ማረፍያ ታህሣሥ 1 ቀን 2001 ዓ.ም.*
*መታሰቢያነቱ ለብላቴ ፀጋዬ ገ/መድህን*